# የኢትዮጵያና ኤርትራ ቅራኔዎች [1]

ከሚንጋ ነጋሽ

የኢትዮጵያና የኤርትራ ጥናቶች ብዙ ጊዜ የሚያተኩሩት፤እንደ ሌሎቹ አፍሪካን የሚመለከቱ ጥናቶች ሁሉ ከነፃነት በፊትና በሁዋላ ስለተፈጠሩ መንግስታትና የፖለቲካ ኢኮኖሚ ስርአት፤ ስለምዐራብያወያን የቀኝ ግዛት ፍለጋ ዘመቻዎችና፤ እንደዚሁም በነዚህ ሀገሮች ዉስጥ ስለሚኖሩ ሰዎች ባህልና ቁዋንቁዋ ነዉ። የፕሮፌሰር ያን አቢንክን የ2010 የኢትዮጵያ-ኤርትራ ጥናቶች ዝርዝር[i] የተመለከተ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ማለትም ከ1995 እስከ 2010 የተሰሩትን ስራዎች ርዕሶች፤ ፀሀፊዎቹንና ጽሁፎቹ የወጡበትን ቦታ፤ጥራትና ተአማኒነት፤ እንደዚሁም ከነዚህ ስራዎች የወጣዉን የእዉቀት መሰረትና መዋቅር (philosophical base & intellectual structure) ለመገምገም እድል ይሰጣል[ii]። ከዚህም በተጨማሪ የምርምር ርአስ ምርጫ፤የጥናቱን የመነሻ ሀሳብ መሰረት፤ የምርመር መንገድ ምርጫ (research design)ና የሚደርሱበትን ድምዳሜ መፈሸ በተለይ ለአዲስ ተመራማሪዎች ይጠቅማል። ይህ ግን የረጅም ጊዜ ስራ ይጠይቃል። በበቂ መረጃና ጽንሰ ሃሳብ ያልተፈተሸ ብሄራዊ ፖሊሲ ዉሎ አድሮም ቢሆን ችግር መፍጠሩ አይቀርም። ብሄራዊ የሆኑ ጉዳዮችን በተለያዩ የእዉቀት መነፅሮችና፤ የልምድ ተመክሮዎች መፈተሽ ወደ ተሻለ የፖሊሲ ንድፈ ሃሳብ እንደሚያሸጋግር ይታወቃል። በዚህም መሰረት ይህ ጽሁፍ የኢትዮጵያንና የኤርትራን ቅራኔዎች በሌላ መነጽር ለማየት ይሞከራል። ለዚህም ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ ነፃና ሚዛናዊ በሆነ ልቦና መገንዘብ ያስፈልጋል።

የሁለቱን ሀገሮች የቅርብ ጊዜዉን ቅራኔ ስንመለከት፤ ከ1961 እስከ 1991 የኤርትራ የተለያዩ ሃይሎች የነፃነት/የመገንጠል ጦርነት ማካሄድና ይህም ጦርነት በኤርትራ አሸናፊነት መጠናቀቁ[iii] ፤ ከ1991 እስከ 1997 በሁለቱ ሃገሮች መሃል የኢኮኖሚ ዉድድር መፈጠሩና ዉጥረት ማምጣቱ፤ ከ1998 እስከ 2000 በሁለቱም ወገን ወደ 500 000[iv] ሰዉ ያሳተፈ የድንበር ጦርነት መደረጉ፤ ከ2000 እስከ አሁን፤ ማለትም እስከ 2015 ቀጥተኛ ጦርነት ባይኖርም በመቶ ሺህ የሚገመት ሠራዊት በያንዳንዱ በኩል ጎራ ለይቶ አንዱ አንዱን እንዳይወረዉ እየተጠባበቀ ይገኛል። የዲፕሎማሲዉና የፕሮፓጋዳዉ ጦርነትም ቀጥሎዋል። በዚህም መሃከል የአንዱ ሃገር መንግስት የሌላዉን ባላንጣ ሲደግፍ ወይም ጠለላ ሲሰጥ ይታያል[v]። የሁለቱ አገሮች ተቃዋሚዎችም ሁኔታዉ እንዳመቻቸዉ አንዱን ተመርኩዘዉ ባላንጣቸዉን ለመግጠም ሲሞክሩ ይታያሉ።[vi] እ.ኤ.አ በ2000 በአልጀርስ የተደረሰዉም ስምምነት እንደተጠበቀዉ የሰላም መሰረት ሆኖ ሊያገለግል አልቻለም። ሁለቱ ሀገሮች ያቁዋቁሙት ኮሚሲዮንም ዉሳኔ በስራ ላይ አልዋለም። የስምምነቱም ዋስ የነበሩት መንግስታት ዉሳኔዉን ማስፈፀም አልፈለጉም።[vii] የነዚህ መንግስታት የቲንክ ታንክ ተቁዋሞችም ሁለቱን ሀገሮች እንዴት እንደሚያወያዩ ሀሳብ ሲነድፉ ይታይሉ። በአጠቃላይ ሁለቱ የኤርትራና የትግራይ ነፃ አዉጪ ሃይሎች በኢትዮጵያ የነበረዉን ማአከላዊ (እነሱ የአማራ የሚሉትን) መንግስት ለማፍረስ የነበራቸዉ ትብብር ወደ ያለመግባባት ተለዉጦ ኤርትራና ኢትዮጵያ በከባድ ቅራኔዎች ዉስጥ ተዘፍቀዉ ይገኛሉ። አዙሪቱ መሰበር እንደሚኖርበት ብዙዎች ቢስማሙም እንዴት መሰበር እንዳለበትና በመፍትሄዉ ላይ ስምምነት የለም። ስምምነት ሊኖር ያልቻለበት አንዱ ምክንያት ቅራኔዉን የሚያስረዳ አጠቃላይ ቀመር በመጥፋቱ ነዉ።[viii]

የቅራኔዉ ተዋንያን መንግሰትና መንግስት ያልሆኑ ሃይሎች (state and non-state actors) ናቸዉ። በአብዛኛዉ መንግስት ያልሆኑ ሃይሎች የተፈጠሩበት ምክንያት በሁለቱ ሀገሮች ያለዉ ኢዲሞክራሲያዊ የአስተዳደር ስርአት ነዉ ። ይህ ጽሁፍ የሚያተኩረዉ በሁለቱ መንግስታት መካከል ስላለዉ ቅራኔ ነዉ። መንግስት ያልሆኑ ሃይሎችን በተመለከተ በጽሁፉ መጨረሻ ላይ ለሰላም ስለሚኖራቸዉ ሚና በአጭሩ ይቀርባል። ብዙዎች በመንግሰታት መሃል የሚነሱ ግጭቶችን ለመፍታት የሚሞክሩት በአለም አቀፍ ድርጅቶች ማለትም የተባበሩት መንግስታትና የአፍሪካ ህብረት ባስቀመጡዋቸዉ መርሆዎች ማለት በሰላም አብሮ መኖር (prinicples of peaceful co-existence) በሚለዉ ሃሳብ ነዉ ። ሆኖም እነዚሁኑ መርሆዎቸ የሚጥሱዋቸዉ መርሆዎቹን ያወጡት ሀገሮች መሆናቸዉን መሳት የለበትም ። ከዚህም በተጨማሪ መርሆዎቹ ለሁሉ ግጭት መፍቻ ፍቱን መድሃኒት ሊሆኑ እንደአልቻሉ ለመረዳት በአለም ላይ ባሁኑ ጊዜ ያሉትን የግዛትና (territories) የድንበር (border) ዉጥረቶች መመልከቱና ለምን መርሆዎቹ እንዳልሰሩ መመርመር ግድ ይላል::[ix]

---

[1] ይህ አጭር ጽሁፍ የተዘጋጅዉ የኢትዮጵያና የኤርትራን የወደፊት ግንኙነት አስመልክቶ እ.ኤ..አ. በጥቅምት 18 2015 በዋሽንግተን ከተማ ተካሄዶ ለነበረዉ ዉይይት ነዉ። በጊዜ እጥረት ምክንያት በስብሰባዉ ላይ አልተነበበም። ጽሁፉ የተጻፈዉ በነጻነትና ማንንም የመደገፍ ወይም የመተቸት አላማ ሳይኖረዉ ነዉ። በዚህ ጽሁፍ አመቶች የተገለጹት በእንደ አዉሮፓ አቆጣጠር ነዉ።

በመንግስታት/በሃገራት መካከል የሚነሱ ቅራኔዎችንና የሚወሰዱትን ዉሳኔዎች በጌም ቲዎሪ (game theory) መመርመር እየተለመደ መጥቶዋል[x]። በሌላ አቅጣቻ ደግሞ የአለም አቀፍ ግጭት አፈታት ቲዎሪስቶች የድንበር ጥሎችን ለመፍታት፤ የቀድሞ ስምምነቶችን (treaties)፤ ጂኦግራፊን፤ ኢኮኖሚን፤ ባህልን፤ ታሪክንና ቦታዉን ማን ይቆጣጠረዉ እንደነበር ለማጥናት ይሞክራሉ። በዚህም ተመርኩዘዉ በሀገሮች መከከል የሚነሱ ቅራኔዎችን ለመፍታት ይሞክራሉ። ለአፍሪካና ለእስያ ሀገሮች ደግሞ ሀገሮቹ ነፃ ሲወጡ የነበሩበትን (uti possidertis) መሬቶች/ግዛቶች ይዘዉ እንዲቆዩ ያሳስባሉ። ይህም አመለካከት አዲስ የወጡ የአፍሪካ ሀገሮች የድንበር ዉጥረታቸዉን ለመፍቻ፤ በሙዋሊሙ ኔሬሬ አሳሳቢነት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በ1963 እንዲቀበለዉ ተደርጎዋል[xi]። እነዚህ መሰረታዊ መመሪያዎች ከኢትዮጵያና ኤርትራ ቅራኔዎች ጋር ያላቸዉ ዝምድና ብዙ ክርክሮች አስነስተዉ እንደነበር ይታወሳል። ፊርማዎችም ተሰብስበዉ ለተባበሩት መንግስታት ጽህፈት ቤት ቀርቦ ነበር[xii]። የኢትዮጵያንም ገዢ ፓርቲ (ህወሃትን) እንደከፈለዉ የሚታወቅ ነዉ። አሁን አዲስ ክርክር መክፈቱ የድንበር ኮሚሲዮኑን ዉሳኔ አይቀይረዉም። ወይም ዉሳኔዉን ተግባሪዊ አያደርገዉም። የአለም አቀፍ ጫና ቢኖርም ዉሳኔዉ በኢትዮጵያ ዉስጥ በነፃ ተመርጦ ስልጣን ለሚይዝ ሃይል ጉዳዩ የጉሮሮ አጥንት እንደሚሆንበት መገመት አያዳግትም።[xiii]

ሆኖም ብዙ የዉጭ ሀገር ጸሃፊዎች የሁለቱን መንግስታት ዉጥረት አሁንም በሁለት ልኡላዊ ሀገሮች መካከል የተደረገ የድንበር ችግር አድርገዉ ይገነዘቡታል። ኤርትራም የተባበሩት መንግስታትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል ስለሆነች ለሰላም መመሪያ ሊሆን የሚችለዉ በሰላም አብሮ መኖር (international principles of peaceful co-existence) ነዉ ይላሉ። አንዳንዶችም በምስራቅ አዉሮፓ አዲስ ነፃ እንደወጡት ሀገሮች ችግር አድርገዉ ይመለከቱታል። በተመሳሳይ በሁለቱም የፖለቲካ መስመር ያሉ የኤርትራና የህወሃት/ኢህአዴግ ፀሃፊዎች የሚከተሉት ይህንኑ የዉጭ ሀገር ጸሃፊዎችን ፈለግ ነዉ። ይህም በ1970ዎቹ የነበሩት የሀሳብ ፍጭቶችና የፖለቲካ መሰመር ልዩነቶች፤ ማለትም (1) ህወሃትና ህግአኤ ለሁለት የተለያዩና ተፎካካሪ ማንነቶች (identity) መዋጋታቸዉና፤ (2) የኤርትራ ጥያቄ የዲኮሎናይዜሽን ወይስ የናሽናል ጥያቄ የሚለዉን ክርክር አቁዋም የመፍትሄ ጎዳና ምርጫ ቅጥያ ነዉ[xiv]። የዛ ተጉዋዳኝ የነበረዉ ደግሞ የሞሪስ ዶብሰን የአዉሮጳ አገሮች ምስረታ ንድፈ ሀሳብ ወደ ኢትዮጵያ አመሰራረት ለማሪዘም የተደረገዉ ሙከራና (replication) የተደረሰበት ኢሳይንሳዊ የሆነ የፖለቲካ ድምዳሜ ነበር።[xv] ይህ የሃሳብ (የማንነት) ልዩነት ዉጤት ዛሬ የምናየዉ ኤርትራ የምትባል የተባበሩት መንግስታትና የአፍሪካ አንድነት አባል የሆነች ሀገር ፈጥሮዋል። የግዛትዋ ስፋትና ወሰኖች ግን እንደሌሎች አዲስ ነፃ እንደወጡ ሀገሮች ሁሉ ከአዋሳኞችዋ ሀገሮች ማለትም ከሱዳን ፤ ከጂቡቲ ፤ ከየመንና ከኢትዮጵያ ጋር ዉጥረት ፈጥሮባታል። በአስተዳደርም በኤርትራ ማእከላዊነትና ሀገር አቀፍ አመለካከትን (centralization, state nationalism) የሚያተኩር አስተዳደር፤ በኢትዮጵያ ደግሞ የዛ ተቃራኒ (አንዳንዶች የቀድሞ የሶቬየት ህብረት ሞዴል የሚሉት) አስተዳደር፤ ማለትም ብሄር ተኮር ፖለቲካና አሰተዳደር (regional/ethnic nationalism) ተዘርግቶ ይገኛል[xvi]። ያም ሆነ ይህ በ1991-1993 በኢትዮጵያ ወስጥ የተከሰተዉ የማእከላዊ መንግስት መፍረስና የህወሃት/አህአዴግ አቁዋም የኢትዮጲያና የኤርትራና ግንኙት በመሰረቱ ለዉጦታል። አዲሱንም ግንኙነት የተወሳሰበ አድርጎታል። የሁለቱም አገሮች የዉስጥ ፖለቲካ ከግዛትና ከድንበር ጋረ ክፉኛ በመቆራኘቱ የአለም አቀፉን መርሆዎችም ሆነ ፍርዶች ለመተግበር በተለይ ለኢትዮጵያ አሰቸጋሪ ሆንዋል ።

በ1989 የተካሄደዉን የአለም የፖለቲካ ለዉጥ ማለትም የሶቪየት ህብረት ከአፍሪካ ቀንድ መዉጣትን ተከትሎ የመጣዉ የ1991ቱ ወታደራዊ ክስተትና እርሱን ተከትሎ የተደረገዉ የፖለቲካ ለዉጥ በሁለቱ ሃገሮች የፈጠረዉ ስሜት በጣም የተለያየ ነበር። በኤርትራ የአሸነፊነት ስሜትና ከዚያ ጋር ተያይዞ የመጣ ተሰፋ ሲሆን በኢትዮጵያ ደግሞ የተሸናፊነትና የሀገር መፍረስ ስሜት ነበር[xvii]። የህወሃት መሪዎችም ቀድሞ የነበራቸዉን መስመር ማለትም የኤርትራ ጸሃፊዎች ያራምዱት የነበረዉን ፈለግ በመከተል፤ኤርትራ እንደ ሊቢያና ሶማሊያ ነፃ የመዉጣት ሙብት አላት ብለዉ፤ ወሰን ሳያሰምሩና የባህር በር ባለቤትነትን ሳያረጋግጡ፤ ለኤርትራ ሙሉ ነፃነት መስጠታቸዉ፤ አሰተዳደሩን የቅምጥ አስተዳደር አሰመስሎት ነበር[xviii]። በ1998-2000 የተፈጠረዉ ወታደራዊዉ ሁኔታ የአሸናፊነቱና ተሸናፊነቱን ስሜት ቢቀይረዉም በህወሃት/ኢህአዴግ አቁዋም ላይ ግን ለዉጥ አልታየም። ሰራዊቱ የነበረዉን የበላይነት ተጠቅሞ ሀገሪቱን የባህር በር ባለቤት ማድረግ አልቻለም። በአሁኑ ጊዜም የኢትዮጵያ መንግስት ትኩረት ከኤርትራ በኩል የሚመጣበትን የመገልበጥ አደጋ በመከላከል፤ የኤርትራን አቀም በመወሰን፤ በአለም ላይ እንድትገለልና ቢቻልም በዚያ ሀገር የመንግስት ለዉጥ በማድረግ ላይ የሚያጠነጥን ፖሊሲ ሲከተል፤ ኤርትራም ይህንን ለማፍረስና የራስዋን ቀመር ለመስራት ስትሞክር ይታያል።

የሁለቱ ሀገሮች ዉጥረት በባድመ ዙሪያ ቢያተኩርም ጉዳዩ ከዚያ በጣም የሰፋ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በድንበር አካባቢ ያሉ ህዝቦችና የወደብ ባለቤትነት መፍትሄ የሚፈልጉ ጉዳዮች ናቸዉ። ሀገራት ሲመሰረቱ ተመሳሳይ ጎሳዎቸ

በሁለትና ከዚያ በላይ ሀገሮች ተከፍለዉ ለመኖር መገደዳቸዉ ሃቅ ቢሆንም፤ በብዙ ሃገሮች ደግሞ ይህዉ መከፈላቸዉ ተመልሶ የግጭት መንስኤ ሆኖ መገኘቱን መዘንጋት የለበትም። ለዚህም በኩርዲስታን፤ካሽሚር፤ ሱማሌ፤ዩክራይና፤አብካዚያ፤ማሲዶኒያ፤ወዘተ ያሉትን ግጭቶችና ዉጥረቶችን ማጤን ይጠቅማል። ወደብን በተመለከተም በአለም ላይ ወደብ ያላቸዉ ሃገሮች ወደብ ከሌላቸዉ ሃገሮች የተሻለ ኤኮኖሚ እንዳላቸዉ የታወቀ ጉዳይ ነዉ። የትራንስፖርት ኤኮኖሚክስ ከልማት ኤኮኖሚክስ ጋረ ያለዉን ብርቱ ቁርኝት በቅጡ መረዳት ያስፈልጋል። ባለፉት 15 አመታት ኢትዮጵያ በሌሎች ወደቦች ለመጠቀም መሞከርዋና አማራጭዋን ማብዛትዋ፤ የኤርትራን ወደቦች የአስፈላጊነት ደረጃ ቢቀንሰዉም፤ 96 ሚሊዮን የሆነዉንና በአመት ወደ 3፥ ያህል የሚያድግን ህዝብን ወደብና ከዛ ጋር የተያየዙ የማንነትና የሴኮሪቲ ጉዳዮችን እዉቅና አለመስጠት ወይም አፍኖ ማስቀመጡ ወደፊት የሚፈነዳን ችግር ለመጭዉ ትዉልድ ትቶ እንደማለፍ መሆኑ ግንዛቤ ሊደረግበት የሚገባ ጉዳይ ነዉ። በስለዚህ የወደቡ ጥያቄ ከኤርትራ ሴኩሪቲ ጋርም ስለሚገናኝ ጉዳዩን በተረጋጋ ሁኔታ ከ"ነፃ ወደብ" ባሻገር መፍትሄ መፈለግና ለህዝቡም ሁኔታዉን ማስተማር እንደ ግጭት መከላከያ ዘዴ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል። በኢትዮጵያም በኩል በጂቡቲ ላይ ያላት መተማመን ምን እያስከፈላት እንደሆነ መመርመር ያስፈልጋል። የሀገሪቱንም ለአደጋ ተጋላጭነት ደረጃ መገምገም ያስፈልጋል። በጂቡቲ ዉስጥ የፖለቲካ ሁኔታዎች ቢለወጡ፤ ለምሳሌ ሀገሪቱ ለአሜሪካና ለፈረንሳይ ያላት አሰፈላጊነትዋ ቢቀንስ ወይም በየመንና በሶማሊያ የሚታየዉ ቀዉስ ቢዛመት፤ ወይም የራስዋ የዉስጥ ችግር ቢባባስ ለኢትዮጵያ ያለዉን እደምታ መገምገምና የረጅም ጊዜ ስትራተጂ መንደፍ ያስፈልጋል። ከኤርትራም ጋር ሰላም መፍጠሩ ኢትዮጵያ ከጅቡቲ በመቆራኘትዎ የተነሳ የሚመጣዉን የአደጋ ተጋላጭነት ደረጃ ይቀንሳል። ስለዚህ የምታደርገዉንም የረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንት ከዚህ አንጻር ማጥናትና ከኤርትራም ጋር የሚፈጠረዉን አዲስ ግንኙነት እንደ አደጋ ተጋላጭነት መቀነሻ (risk hedging instrument) ዘዴ ልትመለከተዉ እንደምትችል መገንዘብ ያሰፈልጋል። ኤርትራም ለዚህ ራስዋን በበቂ ማዘጋጀት ይኖርባታል።[xix]

የሁለቱ ሀገሮች ቅራኔዎች በኢኮኖሚክስ መነጽር ሲታይ፤ የማክሮ ኢኮኖሚ፣ የፊስካልና የገንዘብ ፖሊሲ ልዩነት፤ እንዲሁም በአንድ ገንዘብ ለመጠቀም መሞከራቸዉ፣ የገንዘቡንም ምንዛሪ አቅም በኦፊሴል ማለትም አዲስ አባበና አስመራ ላይ ያሉ የመንግስት ባንኮች (የግል ባንኮች በዛን ጊዜ አልነበሩም) የተለያየ ማድረጉ፤ ኢትዮጲያ ዉስጥ የሚመረቱ የኤክስፖርት እቃዎች ኤርትራ በብር ገዝታ በዶላር መሸጥዋ፤ የቤንዚን ማጣሪያና በኤርትራ የነበሩ የመንግስት የኢኮኖሚ ድርጅቶች ሀብትና እዳ፤ የኤርትራ የዉጭ እዳ ድርሻ፤ በሁዋላም እያንዳንደሩ ሃገር የየራሱን አዲስ ገንዘብ በሚስጥር ማሳተሙ፤ ለግጭቱ ከድንበሩ በላይ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ይታመናል።[xx] በ1998-2000 ጦርነት ተያይዞ ኤርትራዉያን ከኢትዮጵያ በ1991 ደግሞ ኢትዮጵያዉያን ከኤርትራ መባረርና ንብረታቸዉንና ስራቸዉን መቀማታቸዉ፤ በኤኮኖሚ በኩል የተፈጠረዉን ሁኔታ ድርብርብ ያደርገዋል። በሰላም ዉይይት ጊዜ ሁለቱን (ድንበርና ኢኮኖሚን) መለየት እንደሚያስፍልግ የዉጭ ተንታኞች ቢመክሩም[xxi]፤ ሁለቱን መለያየቱ ለያንዳንዱ ሀገር ያለዉን ጥቅምና ጉዳት መሬት በረገጠና በተቻለ መጠን በቁጥር በተደገፈ ዝርዝር ማስቀመጥ ያስፈልጋል። እያንዳንዱ ሀገር ምን ሰጥቶ ምን እንደሚቀበል ለማጤን ይረዳል።[xxii] ብዙዎች የኢኮኖሚ ትንተናዎች የሚሰጡት ከትራንስፖርት ኤኮሚክስና ከገንዘብ አንድነት (monetary union) አንፃር ነዉ። ከነዚህ ባሻገር ያሉትንና ጥቅሞቹም ወዴት እንደሚያጋድሉ በቅጡ መመርመር ያስፈልጋል።

ስምምነት ሲባል ሁለቱም ሀገሮች "አሸናፊ" ሆነዉ የሚወጡበትን መንገድ ማስብ ግድ ይላል። ስምምነት (agreement, MOU, treaty, contract) መፈረም ብቻዉን ዋጋ እንደሌለዉ ከአልጀርስ ስምምነትና አሁን እየተካሄደ ካለዉ የደቡብ ሱዳን ድርድሮች ተመክሮ ማግኘት ያስፈልጋል። በግጭት ሁኔታ ብዙዉን ጊዜ ፖለቲከኞቸ ፊርማ የሚፈራረሙት ዉጥረት ላይ ሲሆኑና ጊዜ ለመግዛት መሆኑንም መረዳት ያስፈልጋል። የፖለቲካ ጌም ቲዎሪ ይህንን ያስተምራል። ስለዚህ የድርድሮች ዉጤቶች ዜሮ ድምር እንዳይሆኑ ሙሉ ሙከራ መደረግ ይኖርበታል። ኤርትራ የተፈረደልኝ ግዛቴ ተይዞብኝ ድርድር አልገባም ስትል ኢትዮጵያ ደግሞ ፍርዱን ብቀበልም ለመተግበር ግን ድርድር ካልተካሄደ መሬቶቹን አለቅም ነዉ የምትለዉ። ይህ የሚያሳየዉ ሁለቱ ባላንጣዎች እርስ በርሳቸዉ አለመተማመናቸዉን ነዉ። ሁለቱም ጥሎ ማለፍ ላይ የተመረኮዘ የዉሳኔ አሰጣጥ ዘዴ ላይ መቀመጣቸዉንም ያመለክታል። ኤርትራ ድርድሩን ተከትሎ የሚመጣ ጥያቄ ስትፈራ ኢትዮጵያ ደግሞ መሬቱን ከለቀቅሁ "አፍንጫሽን ላሺ" እባላለሁ ብላ የምታስብ ይመስላል። ሆኖም ከአለም አቀፍ ህግ አንጻር ሲታይ የኢትዮጵያ አቋዋም የተመሰረተዉ በደካማ መሰረት ላይ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። የኮሚሲዎኑን ዉሳኔ የተቀበለች ከሆነ (ማለትም ባድመን የምትስጥ፤ የወደብ ጥያቄ የማታነሳ ከሆነና ሌላ ተጨማሪ አጀንዳ ከሌላት) ቀሪዎቹን መሬቶች የምትይዝበት ምክንያት ለብዙዎች ግልጽ አይደለም።[xxiii]

በአጠቃላይ በአሁኑ ሰአት ሁለቱ ሀገሮች በንፅፅር ሲቀርቡ፤ ማለትም በአስተዳደር መለኪያ መረጃዎች (Governance Index)፤ በቆዳ ስፋት፤ በባህር ጠረፍ፤ በህዝብ ብዛት፤በጂ.ዲ.ፒ፤ በነፍስ ወከፍ ገቢ፤በወታደራዊ ሃይል፤ በዲፕሎማሲ፤ በተፈጠሮ ሃብትና፤ በሰለጠነ ሰዉ ብዛት፤ወዘተ ሲታዩ ሁለቱም ሀገሮች ድሆች ቢሆኑም፤ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተሽላ የምትታየዉ፤ ሊለማ በሚችል የባህር ሃብትና (marine and off shore resources) ደሴትዎችዋ ለወታደራዊና ለአለም የማሪታይም እንቅስቃሴ በስትራተጂያዊ ቦታ ላይ በመቀመጣቸዉ ነዉ። ይህ ደግሞ ሌላዉ አለም (ሃያላንና የአካባቢዊ ሀገሮች) ሁለቱን ሀገሮች የሚመለከት ፖሊሲ ሲነድፉ ግንዛቤ ዉስጥ የሚያስቀምጡዋቸዉ ጉዳዮች ናቸዉ[xxiv]። እነዚሁ ጉዳዮች በሁለቱ ሀገሮች የወደፊት ግንኙነትና በድርድሮች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የራሳቸዉን ሚዛን መፍጠራቸዉ አይቀርም። የኤርትራም የመወያያ አቀም ከጋራ ኮሚሽኑ ፍርድ፤ የተባበሩት መንግስታትና አፍሪካ አንድነት ድርጅት አባልነትዋ ተጨማሪ በባህር በሮችዋ (ማለትም በሴኩሪቲ) ከዚያም ተያይዞ በሚመጣ ኢኮኖሚ ዙሪያ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ደግሞ ራስዋ ዉስጥ ለማይመረቱ የኤርትራ ምርቶች ገበያዋን በመክፈት፤ ኤርትራዉያን እንደ ቀድሞዉ በኢትዮጵያ እንዲንቀሳቀሱና በቅናሽ ዋጋ እንዲማሩ ማድረግ፤ ኤሌክትሪክና ምግብ በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ፤ የቱሪስት መስመር በመክፈት፤ወዘተ (ማለትም በኢኮኖሚ) ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ሁለቱ ሀገሮች ተለያይተዉ እስከኖሩ ድረስ በሴኩሪቲ፤በልኡላዊነትንና በኢኮኖሚ መካከል የሚደረገዉን ምርጫና እንካ ለእንካ (traede off) ጊዜ ወስዶ መመርመር ያስፈልጋል። የፖለቲካ ፍላጎት (political will) እስካለ ድረስ የስምምነቱ መሰረቶች እነዚሁ ሊሆኑ ይችላሉ። በያንዳንዱም ዘርፍ የሰከነና የሚያመረቃ ጥናት መደረግ ይኖርበታል።

ኤርትራና ኢትዮጵያ ያላቸዉን የሶሺያል ካፒታልና የህበረተሰብ ግንኙት መጠበቁና ማዳበሩ ሊታለፍ የሚገባዉ ጉዳይ አይደለም። ተመሳሳይ ሃይማኖቶችና ብሄር ብሄረ ሰቦች/ጎሳዎች በሁለቱም ሀገሮች ይገኛሉ። እነዚህ ደግሞ በተለያዩ ወቅቶች በአንድ መንግስት ስር የነበሩ ህዝቦች ናቸዉ። ይህ ለወደፊቱ የሁለቱን ሀገሮች ግንኙነት ጤናማ ለማድረግ መሰረት መሆኑን በቅጡ መገንዘብና መንከባከብ ያስፈልጋል። ሌላዉ መታየት ያለበት ጉዳይ የሃያላንና የአካባቢ መንግስታት ከሁለቱ ሀገሮች መተባበርና መጣላት የሚያገኙትና የሚያጡትን ነዉ። ለምሳሌ አሜሪካ የሁለቱን አገሮች መልካም ግንኙት በቀና መልክ ብትመለከተዉ፤ ሩሲያ ተመሳሳይ አመለካከት ላይኖራት ይችላል። አዲሱን የመካከለኛዉ ምስራቅ፤ የየመን፤የሶማሊያንና የደቡብ ሱዳን ቀዉሶች ኢትዮጵያና ኤርትራ በቅርብ የሚከታተሉትና ጣልቃም የሚገቡበት ሁኔታ መኖሩ ይታወቃል። የአዉሮፓ ህብረት (በተለይ እንግሊዝ፤ፈረንሳይ፤ጀርመንና ጣልያን)፤ቱርክ፤ኮዋታር፤ ደቡብ አፍሪካ፤ ቻይና፤ ግብፅ፤ሳዉድ አረቢያ፤እስራኤል ወዘተ በአካባቢዉ ጉዳይ ላይ ትኩረት ሲሰጡ ይታያሉ። ኤርትራም እንደ ጂቡቲ፤ ሶማልያና ሱዳን ሳይሆን እንደ ብራዚል፤ቬኔዝዌላና ህንድ የታዛቢነት ደረጃ በአረብ ሊግ ዉሰጥ ቢኖራትም፤ ይህ በራሱ በአካባቢዉ ጂኦ ፖለቲካ ላይ ይህ ነዉ የሚባል የፈጠረዉ ለዉጥ እስካሁን የለም። የኤርትራና የኢትዮጵያ መንግስታት ይህንን ሁኔታ በጋራ መነፀር ቢመለከቱት ተመሳሳይ ጥቅሞች እንደሚኖራችዉ ግልፅ ነዉ። በዚህም ረገድ ኤርትራና ኢትዮጵያ ሊኖራችዉ የሚችለዉ ትብብር ሰፊና ፈርጅ ብዙ ሊሆን ይችላል።

ለማጠቃለል፤ በቅራኔዉ ዙሪያ ሁለት መንግስታትና ቁጥራቸዉ ያልታወቁ መንግስት ያልሆኑ ሃይሎች አሉ።መንግስት ያልሆኑት ሃይሎች የሲቪክ፤የሰራተኛ፤ የሙያ፤የሃይማኖት፤የጎሳና የፖለቲካ ስብስቦች ናቸዉ። መንግስት ያልሆኑት ሃይሎችም በደጋፊና በተቃዋሚ ይከፈላሉ። ያለፈዉ የ55 አመታት የጦርነትና ቅራኔ ድባቦች መለወጥ እንዳለባቸዉ ስምምነት ቢኖርም መፍትሄዎቹ ቀላል አይደሉም። እነዚህ ሃይሎች የተዋቀሩበት ሂደት የቅራኔዉን የዉጤት አይነት እንደሚወሰነዉ ግልፅ ነዉ። የግዛት፤የድንበር፤የባህር በር፤ የሴኩሪቲ፤የኢኮኖሚ፤ የየሀገሮቹ የዉስጥ ፖለቲካ፤የሶሺያልና የአለም አቀፍ ሁኔታ ውጥንቅጦች ባንድ ላይ ተወሳስበዉ ይገኛሉ። ስለዚህ የኢትዮጲያና የኤርትራ ግንኙነቶችና የግጭት አፈታት ዘዴ ሂደት ከሌሎች አዲስ አገሮች አፈጣጠርና ግጭቶች እንደሚለይ ግንዛቤ ማድረግ ያስፈልጋል። ስለዚህም በአለም ደረጃ የተያዙ መደሃኒቶች ለሁለቱ ሀገሮች ቅራኔዎች ቀጥተኛ ፈዉስ ሊኖኑ እንደማይችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። አለመቻላቸዉም በተግባር እየታየ ነዉ። ከዚህም አልፎ የገላጋይ ኮሚሲዮኖችና የአለም አቀፍ ፍርድ ቤቱ የፈታቸዉን የወሰን ግጭቶችና ክርክሮች በቅጡ መመርመር ያሰፈልጋል። በአለም ላይም ብዙዎቹ የድንበርና የስልጣን ግጭቶች የቆሙት ከተፎካካሪዎቹ አንዱ አሸናፊ ሆኖ ሲወጣ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ከዚህም አልፎ እንደ ሲ.አይ. ኤ ከሆነ በአለም ላይ ያሉ የግዛትና የድንበር ዉጥረቶች ብዙ መሆናቸዉንና በኢትዮጵያና ኤርትራ ብቻ የተወሰነ አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ሀገሮችም በራሳቸዉ የሚያደርጉዋቸዉ ግልግሎች ወደ ተሻለ ዉጤት እንደሚያመሩ እየታመነበት መምጣት ከጀመረ ቆይቶዋል። ስምምነትም የሚደረሰዉ በሁለቱ ሀገሮች መህል በሚደረግ ረጅምና አሰልቺ ዉይይት መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። በሁለተኛ ደረጃ ህብረት እኩል ባልሆኑ ሀገሮች (ማለትም በትንሽና ትልቀ፤በደሃና ሀብታም፤በሃያልና በደካማ፤ ወዘተ) መካከልም ሊፈጠርና ሁለቱንም ሀገሮች

ሊጠቅም ይችላል[xxv]። ከህብረቱም እያንዳንዱ ሀገር የሚያገኘዉን ጥቅም መዘርዘርና መጠኑንና አይነቱን ማወቅ ይጠቅማል። በመጨረሻም ኢትዮጵያንና ኤርትራን በተመለከተ የውጭ ተንታኞች እንደሚሉት የሁለቱ መንግሰታት የገላጋይ ኮሚሲዮኑ ዉሳኔ መተግበር ብቻዉን ቅራኔዉንና የወደፊት የጦርነት ምክንያቶችን (casus belli) እንደማያጠፋ መታወቅ ይኖርበታል። ከዉሴኔዉ በተጨማሪ ወደብ፤ኤኮኖሚ፤ሴኩሪቲና፤የቀይ ባህር ፖለቲካ በሁለቱ ሀገሮች የወደፊት ግንኙት ላይ ተፅቅኖ አላቸዉ። መንግስታዊ ያልሆኑ ስብስቦች ማለትም የሲቪክና የተቃዋሚ ሃይሎችን፤ በተለይ ደግሞ ጠመንጃ ያነሱትን፤ በሰላም ሂደትና በመፍትሄ ፍለጋዉ ፈተና ዉስጥ ማሳተፍ ከጉዳቱ ይልቅ ጥቅሙ እንደሚያመዝን መረዳት ያስፈልጋል።

የግርጌ ማስታወሻዎች

---

[i] http://publications.ossrea.net/index.php?option=com_content&view=article&id=46

[ii] ለምሳሌ የፐሮፌሰር ሺፈራዉ በቀለን የ2011 ግምገማ ይመልከቱ።http://muse.jhu.edu/journals/eas/summary/ v027/27.2.bekele.html

[iii] በሁለቱ አተረጉዋጎም ላይ ያለዉን ልየነት ለመገንዘብ የ1970ዎቹን ክርክሮች መመልከት ይጠቅማል። በአሁኑ ሰአት ግን ወደዛ ክርክር መመለሱ ብዙ ለፖሊሲ የሚያመች ጥቅም የለዉም።

[iv] የአቶ ኢሳያስ አፍወረቂን የሰኔ 1999 የዋሽንግተን ጋዛጣዊ መግለጫ ይመልከቱ።

[v] ይህ ሁኔታ ከ1980ቹ የአፍሪካ ቀንድ ሀገሮች ከተከተሉት ፖሊሲ ጋር ተመሳሳይነት አለዉ። የዚያ ፖሊሲ ዉጤት በደቡብ ሱዳንና በኤርትራ ነፃ መንግሰታት፤ ሶማሊያን ደግሞ መንግስት አልባና የሰሜን ክፍልዋ እንዲገነጠል፤ በኢትዮጵያም ህወሃት መራሽ መንግስት እንዲቁዋቁም አስተዋጽኦ አድርጎዋል። የአሁኑ የኤርትራና የኢትዮጵያ መንግሰታት የሚከተሉት ፖሊሲ ወደ 1990ዎቹ ዉጤቶች እንደማያመሩ የየመንግስታቱ ባለስልጣኖች በኦፊሴል ከሚናገሩት በስተቀር ሌላ ማረጋገጫ የለም። ከዚህም አልፎ በኢትዮጵያም ሆነ በኤርትራ ያለዉ አስተዳደር ኢዲሞክራሲያዊ በመሆናቸዉ እነዚህን መንግስታት ድጋፍ ተደርጎ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ማቁዋቁም አይቻልም የሚል ክርክር አለ። ሰለዚህ የሴራ (conspiracy) ቲዎሪ አለመኖሩና ዲሞክራሲያዊ መንግስታት በሁለቱም አገሮች እንዴት እንደሚመጡ ግልፅ አይደለም። ክርክሩም አልተቁዋጨም።

[vi] የዩሲፍ ያሲንን "የኢትዮ ኤርትራ ጉዳይ፡-ከሰሞኑ ጫጫታ ባሻገር" ይመልከቱ። http://www.ethiomedia.com/1000parts/ serious_assessment.pdf

[vii] በአለም የገላጋይ ፍርድ ቤቶች የተፈቱ የድንበር ግጭቶት ቁጥር ትንሽ ነዉ። ለምሳሌ https://en.wikipedia.org/wiki/ List_of_territorial_disputes ይመልከቱ። የአለም አቀፍ ፍርድ ቤት (International Court of Justice) ስለፈረዳቸዉ ጉዳዮችና የዉሳኔ መንደርደሪያ ጽንሰ ሀሳቦች ግንዛቤ ለማግኘት የብሪያን ሳምነርን Territorial Disputes at the International Court of Justice, Duke Law Journal volume 53 2004 http://scholarship.law.duke.edu/ cgi/viewcontent.cgi?article=1227&context=dlj ይመልከቱ።

[viii] Chatham House፡ Royal Institute of International Relations "Eritrea and Ethiopia: Beyond the Impasse, April 2014, by Jason Mosley.

[ix] በአለ ም ላይ ስላሉ በርካታ የግዛትና የወሰን ቅራኔዎች ዝርዝር የሲ. አ ይ ኤን ድህረ ገጽ ይመልከቱ ። https://www.cia.gov/library/ publications/the-world-factbook/fields/2070.html

[x] ጽንሰ ሀሳቡን ለመረዳት "Game theory and interstate conflict" by Stephen Quackenbush 2014 ይመልከቱ። ተጫዎቾቹ ከሁለት በላይ ሲሁኑና እንዲሁም ተወዳዳሪና ተደጋጋፊ አላማ ሲኖራቸዉ ድምሩ ዜሮ እንደማይሆን መገንዘብ በኤርትራና ኢትዮጵያ ቅራኔን ለማጥናት ይረዳል። ይህ ግን ሌላ ስራ ይጠይቃል።

[xi] http://www.au.int/en/sites/default/files/ASSEMBLY_EN_17_21_JULY_1964__ASSEMBLY_HEADS_STATE__GOVERNM ENT_FIRST_ORDINARY_SESSION.pdf

[xii] ፊርማዉ ከብዙ ድህረ ገፀዎች ተነስቶዋል። ለዚህ ምክንያቱ አይታወቅም። ለናሙና ያህል ግን https://groups.google.com/forum/ #!topic/ soc.culture.ethiopia.misc/WvraI0YvegE ይመልከቱ።

[xiii] ዝኒ ከማሁ። የግርጌ ማስታወሻ ስድሰት፤ ሰባትንና ስምንትን ይመልከቱ። በተጨማሪም በምርጫ ጊዜ የሚነሱ ክርክሮችን፤ የዘዉዴ ረታን "የኤርትራ ጉዳይ 1940-1963"፤ የተከስት ነጋሽን Eritrea and Ethiopia The Federal Experience 1997; የያዐቆብ ሃይለማርያምን "አሰብ የማን ናት" 2003ና የጌታቸዉ በጋሻወን Landlocked-ness as an Impediment to Economic Development in Ethiopia: A Framework for a Durable Solution እና የኪዳኑ አጥናፉና እንዳልካቸዉ ባየህን The Ethio-Eritrean Post-War Stalemate: An Assessment on the Causes and Prospects 2015 ይመልከቱ።.

[xiv] ለምሳሌ የአለም ሰገድ አባይን Identity Jilted or Re-imaging identity? The divergent paths of Eritrea and Tigrean nationalist struggles Red Sea 1998፤ የበረከት ሀብተ ስላሴን "Wounded Nation" 2010: የተስፋ ጽዮን መድሃኔን Towards Confederation in the Horn of Africa Focus on Ethiopia and Eritrea 2010; የዮሴፍ ገብረ ህይወትን The Circular Journey in Search of Eritrea: Journey Identity September 2012 እና Romanticizing Ghedli (I): the Excuses 2008፤ ከመመረቂያ ጽሁፎች ደግሞ የመይላ ተስፋ ሚካኤልን University of London 2011 እንዲሁም የዳንኤል ረዘነ መኮንንን Transitional Justice: Framing a Model for Eritrea, University of Free State 2008 ይመልከቱ።

[xv] Paul Henze's interview with Melez Zenawi C1990. Aavailable at http://asmarino.com/interviews/1722-90-interview-of-meles-zenawi-on-independence-isaias-and-eritreans.

[xvi] ባኢትዮጵያ ያለዉ የፖለቲካ መስመር እንዴት ኤርትራዊነት የሚለዉን የማንነት ጽንሰ ሃሳብ እየተፈታተነዉ እንደሆነ የ ፐ/ር ተስፋ ጽዮን መድሃኔን "ኤርትራ እንደ እናት አገር፤ ችግሮችና ፈተናዎች ትናንትም ዛሬም"፤,የመወያያ ሰነድ 2013ን ይመልከቱ።

[xvii] ለምሳሌ የጆርዳን ገብረ መድህንን የ 1989ና 1993 ጽሁፎች ይመልከቱ።

[xviii] የመለስ ዜናዊን፤ የአብራሃም ያየህን እንዲሁም የገብረ መድህን አርአያን ጽሁፎችንና ንግግሮችን ይመልከቱ። በህወሃት ዉስጥ ሰለነበረዉ ሁኔታ በዝርዝር ለመረዳት የስየ አብራሃንና የገብሩ አስራትን ስራዎች ይመልከቱ።

[xix] ሰለ አዳዲስ ወደቦች የግንባታ ስራ መጀመር የሚከተሉትና ዜናዎች ይመልከቱ። http://www.bbc.com/news/world-africa-17231889. http://capitalethiopia.com/index.php?option=com_content&view=article&id=2142:djibouti-launches-tadjoura-port-construction&catid=35:capital&Itemid=27

[xx] የገብሩ አስራትን "ሉዓላዊነትና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ መጽሃፍ (2006) ይመልከቱ።

[xxi] ዝኒ ከማሁ።

[xxii] ኢትዮጳያ ያላትን ምርጫዎች ለመገንዘብ “Time to bring back Eritrea from the cold: A reply to Ambassador Hank Cohen” http://www.ethiomedia.com/14store/5620.html ይመልከቱ።

[xxiii] የተሰጡትን መሬቶች በ http://news.bbc.co.uk/2/hi/africa/4548754.stm ይመልከቱ።

[xxiv] ኢትዮጵያ በሶማሊያ ጉዳይ፤ ኤርትራ ደግሞ በየመን ጉዳይ በቀጥታ መግባታቸዉን በተባበሩት መንግስታት ሪፖርቶቸ ላይ መመልከት ይቻላል። http://www.un.org/ga/search/view_doc.asp?symbol=S/2015/802

[xxv] አንዳንዶች ከኤርተራ መወዳጀት እንደገና አይቻልም ይላሉ። በመንገፍገፍም ከጥቅሙ ጣጣዉ ያመዝናልና አሁን ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ የተሻለ ነዉ ይላሉ። ይህ ድምዳሜ ከጭንቀት የመነጨ መሆኑን መገንዘብ ያስፍልጋል።